DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

## ከትምህርት በኋላ የሚሰጥ ፕሮግራም

በትምህርት ዓመት 2020-2021፤ ከትምህርት ግዜ ውጪ በሚሰጥ ፕሮግራም (Out of School Time Programs (OSTP) የሚተዳደረው ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም (afterschool programs) በ 55 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይሰጣል። ከትምህርት ግዜ ውጪ በሚሰጥ ፕሮግራም የማይተዳደሩ፣ የራሳቸውን ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም ለተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ከልጅችዎ ትምህርት ቢቶች ጋር ተነጋገሩ።

ከትምህርት ግዜ በኋላ በሚሰጠው ፕሮግራም ለመሳተፍ የሚደረገው ምዝገባ ሓምሌ 20 ቀን 2012 ዓ.ም (July 27th, 2020) ይጀምራል። አዲስ ነገር ካለ ለማወቅ ከፈለጉ ዌብሳይቱን ይመልከቱ። በትምህርት ቤቱ፤ በትምህርት ዓመት 2020-2021 ለመሳተፍ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ምዝገባው በኦንላይን ይከናወናል ።

**የትምህርት ዓመት 20-21 የከትምህርት በኋላ ምዝገባ ሓምሌ 20 ቀን 2012 ዓ.ም (July 27th, 2020) ይጀመራል፡፡ በዚህ ከትምህርት በኋላ በሚሰጠው ፕሮግራም ከመመዝገብ በፊት፤ በዛው ትምህርት ቤት ወስጥ በትምህርት ዓመት 2020-21 ለመማር ተማሪው የተመዘገበበትን ወረቀት መጀመርያ ማቅረብ አለበት።.** ይህም ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም የሚደረግ ለውጥ አስፈላጊው መረጃ እንዲኖሮት የዚህን ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም ዌብሳይት በቅርቡ እንድትከታተሉና የቦታ ጥበት ሊይጋጥም ስለሚችል በተቻለ መጠን በተቀላጠፈ ሁኔታ ልጅን እንዲያስመዘገቡ እናበርታታለን።

### ከትምህርት በኋላ የሚሰጥ ፕሮግራም መግለጫ



**ከትምህርት ግዜ በኋላ የሚሰጥ ፕሮግራም ምን ያበረክታል?**

የዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (DC Public Schools (DCPS) ከትምህርት ግዜ በኋላ የሚሰጠው ፕሮግራም ተማሪዎች በአካዳሚ ትምህርትና ከትምህርት ግዜ ውጪ በሚሰጡ ትምህርቶች እንዲሳተፉ፣አዳዲስ የሚወዷቸውን ነገሮች እንዲማሩና ሙያዎች እንዲቀስሙ ያደርጋል፡፡ የዲሲ አስተማሪዎች፡ ባለሙያዎችና የማህበረሰቡ ክፍሎች ልዩ የሆኑ ምርጫዎችን ለተማሪዎች ያቀርባሉ፡፡

ጥሩ በሆነ የከትምህርት በኋላ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ፤ ተማሪዎች ለትምህርት ያላቸውን ተቀባይነት እንዲያጎለብቱ፣ በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት እንዲያገኙ ፤ ከትምህርት የሚመረቁ የተማሪዎችን ቁጥር ከፍ እንዲል፤ ተማሪዎች በትምህርት ላይ ያላቸው አስተያየት እንዲሻሻል እንደሚያደርግ ተረጋግጧል፡፡ ተማሪዎች ዕለታዊ መደበኛ ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚወስዷቸው የከትምህርት በኋላ የሁለት ሰዓት ተኩል የተለያዩ ትምህርቶች፤ በአጠቃላይ መደበኛ ትምህርታቸውን ለሁለት ወራት ወስደው ከሚቀስሙት እውቀት ጋር የሚመጣጠን ነው ተብሏል፡፡

**የከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች የሚሰጡባቸው ሰዓታት መቼ ናቸው?**

ከትምህርት በኋላ የሚሰጡት ፕሮግራሞች በየቀኑ ልክ የቀኑ የትምህርት ግዜ ሲያበቃ ይጀምሩና እስከ 6:15 ድረስ ይቆያሉ።(በትምህርት ቤቱ አንዳች ለውጥ እስካልተደረገ ድረስ)

**የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው በነዚህ ከትምህርት በኋላ በሚሰጡት ፕሮግራሞች ለመሳተፍ የሚችሉት?**

በእነዚህ ከትምህርት በኋላ በሚሰጡት ፕሮግራሞች፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከቅድመ-ኪንደርጋርተን 3 (PK3) ጀምሮ እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ ያሉት ተማሪዎችና በሌሎች የትምህርት ተቋሞች ከቅድመ-ኪንደርጋርተን 3 (PK3) ጀምሮ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ያሉት ተማሪዎች ሊሳተፉ ይችላሉ።

**ምግብ ይሰጣል?**

እስከ ራት ድርስ የሚጠቅማቸው ማቆያ ምግብ ይሰጣቸዋል።

**ልጆቼን እንዴት ነው ማስመዝገብ የምችለው?**

- **ከትምህርት በኋላ በሚሰጡት ፕሮግራሞች ለመካፈል ምዝገባው በኦንላይን ነው። የሚጀመረው ደግሞ በሓምሌ ወር ነው።** ይህንን የኦንላይን ምዝገባ የሚያደርጉ ቤተሰቦች፡ ፕሮግራሙ፣ ምን ያህል የእያንዳንዱ ልጅ ፍላጎት ግምት ውስጥ ገብቶ የተዘጋጀ ፕሮግራም መሆኑን ትምህርት ሊቀስሙበት ይችላሉ።**ይህንን የኦንላይን ምዝገባ ለማካሄድ የእጅ ስልኮን ወይም የቤትዎን ስልክ አይጠቀሙ፣ ኮምፑተር ነው መጠቀም ያለቦት።** እቤትዎ ኮምፑተር ከሌሎት ደግሞ በምዝገባው ወቅት፣ ከጥዋቱ 9 ሰዓት እስከ ቀኑ 3 ድረስ የልጅዎ ትምህርት ቤት ወስጥ በመምጣት ኮምፑተር ሊጠቀሙ ይችላሉ። የዲሲ የመንግስት መጻህፍት ቤቶችም ኮምፑተሮች ስላሏቸው እዛም ሊሄዱ ይችላሉ።
    - ሰዓታትና ቦታዎች
- ወደ መጽሐፍት ቤት (Library) መመለስ፡ ደህነንቱ ወደተጠበቀ እንደገና መከፈት (Reopening) የምናደርገው ጉዟችን

  https://www.dclibrary.org/reopen
- **በኦንላይን የሚደረገው ምዝገባ አንዴ ከተጀመረ በኋላ፣** ልጆች እንድየአመጣታቸውና አመዘጋገባቸው ነው ቦታ የሚኖራቸው።ያለው ቦታ የተወሰነ ነው፣ ቶሎ የተመዘገቡት ቦታ ይኖራቸዋል። ስለዚህ ቦታ ለማግኘት በግዜ መመዝገብ ያሻል።
- **የ ምዝገባው ሂደት በጣም ስለተቃለለ፣ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች አንዴ በኦንላይን የሚደረገውን የምዝገባ ፎርም ካገባደዱ በኋላ፣ ተጨማሪ ዶኩመንቶችን ማቅረብ አይኖርባቸውም።**
- **በ2020-21 የትምህርት ዓመት በትምህርት ቤቱ ለመማር ከተመዘገቡ በኋላና መረጃው ወደ ትምህርት ቤቱ የኮምፑተር መዝገብ እንዲገባ ሁለት የስራ ቀናት ካለፉ በኋላ ነው ከትምህርት በኋላ በሚሰጠው ፕሮግራም መመዝገብ የሚችሉት።** ስለ 2020-21 የትምህርት ዓመት ምዝገባ **ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።**
- ማንኛውም ተማሪ ከትምህርት በኋላ የሚሰጠውን ፕሮግራም ምዝገባ ካላጠናቀቀ በፕሮግራሙ ሊካፈል ፍጹም አይችልም።

**ለመመዝገብ ችግር ካጋጠመኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?**

ከልጆዎ ትምህርት ቤት ጋር ተገናኙ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 442-5002 በመደወል ከትምህርት በኋላ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት ዘንድ ደውለው እርዳታ ይጠይቁ።

**የሚከፈል ገንዘብ አለ?**

ለትምህርት ዓመት 20-21 የሚከፈለው ገንዘብ ለስምንት ተከታታይ ወራት(ከ ጥቅምት አንድ ቀን 2020 እስከ ግንቦት 30 ቀን 2021) ሆኖ፤ በአንድ ቤት ውስጥ ላሉ ልጆች- የመጀመርያው ልጅ በየወሩ $94.50 መከፈል ሲኖርበት፣ ሁለተኛው ልጅ ግማሽ ማለትም $47.25 ይከፍላል፣ ሶስተኛው ልጅም ሆነ በቤተሰቡ ያሉ የተቀሩት ልጆች ግን ነጻ ናቸው፣ ምንም አይከፍሉም። የኦ-ኤስ-ቲ-ፒ( OSTP) የከትምህርት ግዜ በኋላ ፕሮግራም ግን ከዚህ በታች በተዘረዘሩ ጉዳዮች በአንድ ወይም ከዛ በላይ በሚገኝ ክልል የሚገኙ ቤተሰቦች ነጻ ነው፤

- ለችግረኛ ቤተሰቦች በሚሰጥ ግዚያዊ እርዳታ (TANF ) ወይም በሜዲኬድ ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦች ፕሮግራሙ ነጻ ነው።
- ቤት-አልባ የሆኑ ተማሪዎች፡ የሚይዛቸው የሌላቸው ልጆች ወይም በጥገኝነት ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር የሚኖሩ ልጆች ፕሮግራሙ ነጻ ነው።
- በመካከለኛው የትምህርት ደረጃ(በሃርት( Hart ) እና ጄፈርሰን (Jefferson) ለሚገኙ ተማሪዎች ፕሮግራሙ ነጻ ነው።
- የተመደበውን ገንዘብ ለመክፈል እንደማይችሉ የገቢያቸውን መጠን የሚያሳይ ወረቀት ያቀረቡ ቤተሰቦችም ነጻ ፕሮግራም ሊያገኙ ይችላሉ።
- እንደንቡ ከሆነ በታንፍ (ለተቸገሩ ቤተሰቦች የሚሰጥ ግዚያዊ እርዳታ- TANF)ም ሆነ በሜዲኬድ ለመግባት ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ግን በአሜሪካን አገር ህጋዊ የመኖርያ ፍቃድ ስለሌላቸው እንኚህን ጠቀሜታዎች ሊያገኙ አይችሉም።ግን በፕሮግራሙ ውስጥ ልጆቻቸውን በነጻ፣ ካለ ክፍያ ሊያስገቡ ይችላሉ።

በተዘጋጀው አዲስ የአከፋፈል ሁኔታ በኦንላይን ለመክፈል የሚፈልጉ ቤተሰቦች፣ በኦንላይን afterschoolpayment.dcps.dc.gov ውስጥ በመግባት በተረጋገጠ ቼክ (Certified checks)፣ በካሸር ቼክስ (cashier's checks) ወይም በገንዘብ ትእዛዝ (money orders) ለመክፈል ይችላሉ። የግል ቼኮችን ግን አይቀበሉም።

**ይህ ከትምህርት በኋላ የሚሰጥ ፕሮግራም በእንዴት አኳሃን ነው የሚገመገመው?**

የ ትምህርት ዓመት18-19 21ሲ-ሲ-ኤል-ሲ (21CCLC) የዓመት መጨረሻ ግምገማ ሪፖርት፣ በኦ-ኤስ-ኤስ-ኢ (OSSE) እና በዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ( DCPS ) በተሰጡ ግቦች መሰረት፡ የፕሮግራሙ ዋነኛ ዓላማዎች ምን እንደሆኑ በዝርዝር ያቀርብና እነኚህ ዓላማዎች በትምህርት ዓመት 2018 - 2019 ግባቸውን መቱ ወይስ አልመቱም የሚለውን ጥያቄ ይገመግማል። በተጨማሪም፣ሪፖርቱ፣ ስለ 21CCLC የተሰጡ ሽልማቶች( grant)፣ የፕሮግራሙ አካሄድ፡ ከውጭ ገምጋሚዎች የተሰጡ ግኝቶች ፣ የከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች ጥንካሬና በትምህርት ዓመት19-20 ትኩረት የተሰጣቸውን ጉዳዮች በዝርዝር ያቀርባል። ስለዚሁ ጉዳይ ያሎትን ጥያቄዎች ለማርጎ በርኪ( Margot Berkey)፣ የ21ሲ-ሲ-ኤል-ሲ (CCLC) ሽልማት ባለሞያ በኦንላይን ወደ margaret.berkey@k12.dc.gov በመግባት ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ድርጅቶች ስለ ዲሲ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች የተሰጠ መረጃ**

ከትምህርት በኋላ ስለሚሰጡ ትምህርቶች/ፕሮግራሞች ጥያቄ ቢኖሮት ወደ ሚከተለው ይደውሉ፣

**ከትምህርት በኋላ የሚሰጡ ፕሮግራሞች፡ (202) 442-5002**